# የደረጃ 1 መመሪያ

## ኮሮና ቫይረስ 2019 (COVID-19) የጥርስ ህክምና መቼቶች መመሪያ

በደረጃ 1 ወቅት ህዝቡ እና የተለያዩ ቢዝነሶች ለሁሉም የተጋላጭነት መጠን ቅነሳ ሲባል አዳዲስ ባህሪያትን እና ጠንከር ያሉ የመከላከያ ልማዶችን እንዲያዳብሩ ይጠየቃሉ። ይህ መመሪያ በደረጃ 1 ወቅት የጥርስ ጤና አጠባበቅ አቅራቢዎች (DHCP) ድንገተኛ ያልሆኑ የጥርስ ሕክምና አገልግሎቶችን እንዲሰጡ ለመምራት ታስቦ የተዘጋጀ ነው ፡፡ አገልግሎቶችን የሚያቀርቡ ከሆነ በሠራተኞች ፣ በደንበኞች እና በማህበረሰቡ መካከል የ COVID-19 ስርጭትን ለመቀነስ የሚከተሉትን እርምጃዎች መተግበር አለባቸው ፡፡ ለበለጠ መረጃ coronavirus.dc.gov/phaseone ን ይጎብኙ።

## ለታካሚ የሚሰጥ አትኩሮት

- አገልግሎት ሰጭዎች በክሊኒክ አመቺ በሚሆኑበት ጊዜ አቅራቢዎች አማራጭ የሕክምና አሰጣጥ ሞዴሎች፣ ቴሌዴንታል ቴክኖሎጂን ጨምሮ በቀጣይነት ከግምት ውስጥ ማስገባት አለባቸው ፡፡
- አፋጣኝ የእንክብካቤ እና የፊት-ለፊት ንግግር የጤና እንክብካቤ አስፈላጊነት ላይ በመመርኮዝ አስፈላጊ የሆነውን ተመራጭ የጥርስ ህክምና ለመከፈት ቅድሚያ ይስጡ ፡፡
- ከ COVID-19 ጋር ተዛማጅ የሆኑ ምልክቶች ያሉዋቸዉ እንደሆነ ሁሉንም ሕመምተኞች በስልክ ያጣሩ ፡፡ ታካሚው የ COVID-19 ምልክቶች እንዳሉት ያሳወቀ እንደሆነ ድንገተኛ ያልሆኑ የጥርስ ህክምናዎች እንዲዘገይ ማድረግ ፡፡
- ለሁሉም ታካሚዎች እና ጎብኝዎች እንደደረሱ ግምገማ ማካሄድ ፡፡ አንድ ታካሚ ትኩሳት ወይም ከ COVID-19 ጋር ተዛማጅ የሆኑ ምልክቶችን ካሳየ ፤ ድንገተኛ ያልሆኑ የጥርስ ህክምናዎች መዘግየት አለባቸዉ ፡፡
- ታካሚዉ እና ጎብኝዎች ህክምና በማይወስዱበት ጊዜ የፊት ጭምብሎች ማድረጋቸዉን ማረጋገጥ ፡፡

## የድርጅቶች አትኩሮት

- ማንም ትኩሳት ወይም የ COVID-19 ምልክት ያለበት ሰው ወደ ተቋሙ መግባት እንደማይችል የሚገልጽ ምልክት ይለጥፉ።
- ከ 60 - 95% የአልኮል ይዘት ያለዉ የእጅ ማፅጃ (ABHR) ፣ ሶፍት እና በእጅ የማይነኩ የቆሻሻ መጣያዎች ጨምሮ በጤና ተቋማት መግቢያዎች ላይ ፣ በመጠባበቂያ ክፍሎች ፣ እና በታካሚዎች ምርመራ ክፍል ውስጥ ለተገቢ የመተንፈሻ ንጽህና እና ለሳል ጥንቃቄ የሚረዱ አቅርቦቶችን ማዘጋጀት ፡፡
- በተጠባባቂ ግለሰቦች እና ኢንፌክሽኑን ሊያስተላልፉ የሚችሉ ታካሚዎች መካከል የሚኖረዉን የጠበቀ መቀራረብን ለማስቀረት በመጠባበቂያ ስፍራዎች የሚያለያዩ ነገሮች (ለምሳሌ ፣ የመስታወት ወይም የፕላስቲክ መስኮቶችን) ማሰናዳት ፡፡
- በመጠባበቂያው ክፍል ውስጥ ሆነው የሚጠብቁ ሰዎችን ብዛት ማሳነስ ፡፡
  - ታካሚዎች ለጥርስ ህክምና ተራቸዉ በሚደርስበት ጊዜ በሞባይል ስልክ ሊጠሩ የሚችሉበት ስፍራ በግል መኪና ውስጥ ወይም ከጥርስ ህክምና ተቋሙ ውጭ መሆንን መምረጥ ይችላሉ ፡፡
  - ተደራራቢ የጥርስ ህክምና ቀጠሮዎችን መቀነስ።
- የጥርስ ህክምና መሣሪያዎች ጥቅም ላይ ሳይውሉ ከቆዩበት ጊዜ በኋላ ተገቢ እና አስፈላጊ ጥገና ማግኘታቸውን ያረጋግጡ።

## የአገልግሎት  አትኩሮት

- አገልግሎቱ ተለዋዋጭ ፣ ለቅጣትን ያልሆኑ እና ከህዝብ ጤና መመሪያ ጋር የሚጣጣሙ የህመም ፈቃድ ፖሊሲዎች ለ DHCP ም መተግበር አለበት፡፡
- ታካሚዎች በ 14 የጉብኝት ቀናት ውስጥ የCOVID-19 ምልክቶች የታዩባቸው እንደሆነ ለ DHCP እንዲያሳውቁ መጠየቅ አለባቸው ::
- ከ COVID-19 ጋር የሚዛመድ ትኩሳት እና የሕመም ምልክቶች የሚታዩባቸዉ እንደሆነ DHCP እራሳቸውን በየጊዜው ክትትል እንዲያደርጉ መጠየቅ አለባቸዉ ::
- DHCP በሚታመሙበት ጊዜ አገልግሎት መስጣት የለባቸዉም :: በሥራ ላይ እያሉ ከታመሙ ወዲያውኑ እንክብካቤ መስጠታቸውን በማቆም አሠሪዎቻቸውን ማሳወቅ ፣ ከዚያም ተቋሙን ለቀው በመውጣት ከጤና አጠባበቅ ባለሙያዎቻቸው ጋር መማከር አለባቸው ::

## የኢንፌክሽን ቁጥጥር እና የግል የመከላከያ መሣሪያዎች

- DHCP በአንድ ጊዜ ለአንድ ታካሚ የክሊኒካል ህክምዉን መገደብ አለበት ፣ የሚቻል ከሆነም ታካሚዎቹን በተናጥል በህክምና ክፍሎች ውስጥ ማስገባት :: ይህ የማይቻል ከሆነም የሚለያዩአቸዉ ነገሮች ኖረዉ ታካሚዎች የ6 ጫማ ያክል አካላዊ ርቀት ሊኖራቸዉ ይገባል ::
- አገልግሎት እየሰጡ የሌሉ ሁሉም አቅርቦቶችን እና መሳሪያዎችን በተከደኑ ማስቀመጫዎች እንደ መሳቢያዎች እና መደርደሪያ ሳጥኖች ውስጥ መደረግ እና ከሚበክሉዋቸው ነገሮች ንክኪ መራቅ አለባቸው :: በሂደቱ ወቅት የተጋለጡ ነገር ግን ያልተጠቀሙባቸውን ማንኛዉንም አቅርቦቶች እና መሳሪያዎች እንደ ተበከሉ መወሰድ አለባቸው እና ሂደቱ ካበቃ በኃላ በትክክል መጣል ወይም በድጋሚ ጥቅም ላይ ለማዋል መፀዳት አለበት ::
- DHCP በተለይም ማንኛውንም የታካሚ ህክምና ከመጀመሩ በፊት እና በኋላ ፣ ከአስተላላፊ ቁስ አካላት ጋር መነካካት እንዲሁም የግል መከላከያ መሳሪያዎች (PPE) ጓንትን ጨምሮ ከመልበስ በፊት እና ከማዉለቅ በኃላ ጥብቅ ሆነ የእጅ ንጽህናን መተግበር አለበት ::
- DHCP በማንኛውም ጊዜ የቀዶ ጥገና ጭንብል መልበስ አለበት ፣ በተጨማሪም የዓይን መከላከያ (መነፅር ፣ ጠንካራ ዓይን ላይ የሚደረግ የጎን መሠፈኛ ወይም ሙሉ የፊት ጋሻ ያለው መከላከያ)፣ ጓንት እና ጋዎን የደም ወይም የሌሎች የሰውነት ፈሳሾች የማፍለቅ ወይም የማፍሰስ ሁኔታ ሊያስከትሉ በሚችሉበት ሂደቶች ወቅት እንዲረዱ መለበስ አለባቸው ::
- በሚቻልበት ጊዜ ሁሉ አየር-ማመንጨት(aerosol-generating) ሂደቶችን ያስወግዱ። እንደነዚህ ዓይነቶቹ ሂደቶች አስፈላጊ ከሆኑ DHCP ከላይ ከተዘረዘሩት ሌሎች የግል መከላከያ መሳሪያዎች (PPE) በተጨማሪ ከጭምብል ይልቅ የ N95 የመተንፈሻ መሳሪያን መልበስ አለበት :: የመተንፈሻ መሳሪያዎች የህክምና ግምገማዎችን ፣ ስልጠናዎችን እና ተገቢ ምርመራን የሚያካትቱ በመተንፈሻ አካላት ጥበቃ ፕሮግራም ውስጥ ጥቅም ላይ መዋል አለባቸው።
- የቀዶ ጥገና ጭምብል እና የሙሉ ፊት መሸፈኛ ከሌለ ምንም የአየር-ማመንጨት(aerosol-generating) ሂደቶችን አያከናውኑ ::
- ለ PPE መልበሻ እና ማዉለቂያ የሚሆኑ ስፍራዎች፣ እንዲሁም ለ PPE ማስወገጃ የሚሆኑ ቆሻሻ መጣያዎች በሁሉም የታካሚ ክፍሎች ዉስጥ መዘጋጀት አለባቸው ::
- በማስወገድ ወቅት ወደ ባዶ እጆች ሊተላለፉ የሚችሉትን ማንኛውንም በሽታ አምጪ ተወስያንን ለማስወገድ በየታካሚ PPE ን መቀየር፣ እንዲሁም PPE ከመልበስ በፊት እና ከማዉለቅ በኃላ የእጅ ፅዳት መተግበር አለበት ::

- DHCP የመተንፈሻ መሳሪያን ወይም የቀዶ ጥገና ጭምብሉን በማስወገድ ተቋሙን ለቀው በሚወጡበት ጊዜ የጨርቅ ፊት መሸፈኛቸውን ማድረግ አለባቸው ::

## ማጽዳት እና ከበሽታ አምጪ ህዋሳት ነፃ ማድረግ

- ከእያንዳንዱ ታካሚ ህክምና በኋላ DHCP የአካባቢ ጽዳት እና ከበሽታ አምጪ ህዋሳት ነፃ የማድረግ ሂደቶች በተከታታይ እና በትክክል መከተላቸውን ማረጋገጥ አለበት ::
- በ COVID-19 በሽታ ያልተጠረጠሩ ወይም መያዛቸዉ ያልተረጋገጠ እያንዳንዱ ታካሚ አገልግሎት አግኝተው ከወጡ በኋላ ክፍሉን ማፅዳትና ከበሽታ አምጪ ህዋሳት ነፃ ማድረግ ለመጀመር ከጥርስ ህክምናዉ ሂደት በኋላ በአየር ላይ ያለ እርጥበት በደንብ እስኪወርድ ድረስ ለ 15 ደቂቃዎች ያክል ይጠብቁ ::
    - በCOVID-19 በሽታ ለተያዘ ታካሚ የአስቸኳይ ጊዜ ሕክምና የሚደረግለት ከሆነ፣ እንፌክሽን አስተላላፊ ሊሆኑ የሚችሉ ቅንጣቶች ለማስወገድ በቂ የአየር ለውጦች እስኪደረጉ ድረስ DHCP ወደ ቀዶ ጥገናው ሳይገባ መቆየት አለበት ::
- እለታዊ የጽዳት እና ከበሽታ አምጪ ህዋሳት ነፃ የማድረግ ሂደቶች (ለምሳሌ ፣ አብዘኛዉን ጊዜ የሚነካኩ ነገሮችን ወይም ቁሳቁሶችን በምርት የአጠቃቀም መመሪያ ላይ በተጠቀሰዉ መሰረት ከበሽታ አምጪ ህዋሳት ነፃ ለማድረግ ማፅጃዎችን እና ውሃን በመጠቀም አስቀድሞ መፅዳት) በመጠቀም የታካሚ አገልግሎት መስጫ የአየር-ማመንጨት(aerosol-generating) ሂደቶች የሚከናወኑባቸው ክልሎችን በማካተት የጤና እንክብካቤ መቼቶች ለ SARS-CoV-2 ተገቢ ናቸው ::
    - ስለ የ SARS-CoV-2 ለማጥፋት የሚጠቅሙ በ EPA የበሽታ አምጪ ተህዋስያን መርሃግብር ለተረጋገጡ በ EPA የተመዘገቡ ከበሽታ አምጪ ህዋሳት ነፃ የማድረጊያ ምርቶች በ EPA ድህረገጽ ላይ የ N ዝርዝርን ይመልከቱ ::

## የግንባታ አትኩሮቶች

- የአየር ማናፈሻ ስርዓቶች በአግባቡ መስራታቸዉን እና በተቻለ መጠን ዝውውር እንዲጨምር የተዋቀሩ መሆናቸውን ማረጋገጥ :: ተገቢ ለሆኑ የማዋቀር አማራጮች ዝርዝር መመሪያ በ CDC ድረገፅ ላይ የጥርስ ህክምና መቼት መመሪያን ማግኘት ይቻላል፡ cdc.gov/coronavirus/2019-ncov/hcp/dental-settings.html#EngineeringControls
- የቆሸሸ ውሃን ለማፅዳት እና በንጹህ ውሃ ለመተካት የውሃ ስርዓቶች እንዲታጠቡ ያድርጉ፡፡ ይህ ውሃው ውስጥ ሊገባ የሚችልን ማንኛውንም ብረት (ለምሳሌ፡ ሊድ) ያስወግዳል እንዲሁም ተጋላጭነት ይቀንሳል ለ Legionnaires በሽታ እና ከውኃ ጋር የተዛመዱ ሌሎች በሽታዎች፡፡ እርምጃዎች ለዚህ ሂደት በ CDC ድረ ገፅ ላይ ሊያገኙ ይችላሉ፡ cdc.gov/coronavirus/2019-ncov/php/building-water-system.html.

የበለጠ የመመሪያ ዝርዝር በ CDC የጥርስ ህክምና መቼት መመሪያ ላይ ሊገኝ ይችላል፣
cdc.gov/coronavirus/2019-ncov/hcp/dental-settings.html. የ መመሪያዎቹ ከላይ ያሉት ወረርሽኙ እየተስፋፋ በሄደ ቁጥር እየተሻሻሉ ይሄዳሉ። እባክዎን coronavirus.dc.gov ለወቅታዊ መረጃ በመደበኛነት ይጎብኙ።